# የምጽአቱ የምሥራች

ቅጽ 74 ቁጥር 3 (879) "በመከራ ቀን ጥራኝ አድንህማለሁ አንተም ታከብረኛለህ" *መዝሙረ ዳዊት 49፥15*



በጂም ኪምባላ የቀረበ


## የሰማያት መስኮቶችን የሚያስከፍት ጸሎት

የእግዚአብሔር ቤተሰቦች በየዘመናቱ ብርቱ ችግር ሲገጥማቸው ለእግዚአብሔር ጸሎት እያቀረቡ መፍትሄ አግኝተዋል፡፡ ሀና ልጅ የሌላት መካን በመሆኗ በሌሎች ሴቶች ዘንድ መሳቂያ ስትሆን ወደ ቤተመቅደስ ገብታ ካህኑ ኤሊ በስካር የምትለፈልፉ እስኪመስለው ድረስ ፀለየች፡፡

እግዚአብሔርም ፀሎቷን ሰምቶ ታላቅ የሆነውን ነብይ ሳሙኤልን እንድትወልድ አበቃት እርሱም በእግዚአብሔር ቤት ታላቅ አገልጋይ ሆኖ የእግዚአብሔር ህዝቦችን ከብዙ ጥፋት እንዲተርፉ መልክተኛ ሆነ፡፡

(መጽሐፍ ሳሙኤል ቀዳማዊ 1:7-28)

በአዲስ ኪዳንም የክርስቶስ ኢየሱስ ተከታይ አማኞች ብርቱ ፀሎት በሚያደርጉበት ወቅት እግዚአብሔር ከባድ ፈተናዎችንና የሠይጣን ወጥመዶችን እየሰባበር ሕዝቦቹን ከድል ወደ ድል አሸጋግሯል፡፡

ቤተክርስቲያንም በጣት ከሚቆጠሩ አባላትና ተከታዮች ወደብዙ ሚሊዮን ቢሊዮኖች አባላትን አፍርታለች፡፡

(የሐዋርያት ሥራ 2÷2 9÷40 16÷25)

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሐና የፀለየችውም ሆነ የጌታ ደቀመዛሙርት በአዲስ ኪዳን ዘመን የፀለዩት ተገቢና ትክክለኛ ጸሎት ስለነበር እግዚአብሔር ጸሎትን ሰምቶ በጎ መልሱን ሰጥቷል፡፡የፃድቃን ጸሎት ጌታን የሚያስከብር ለሰዎች መዳንና በጎነት በመሆኑ እግዚአብሔር ይሰማዋል፡፡ (ያዕቆብ 5÷16)

ዛሬስ በዘመናችን በእግዚአብሔር የተጠራን የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በመንፈስ ቅዱስ የምንመራ ጸሎታችን ይሰማናል? መልሱ አዎን ነው ምክንያቱም ቅዱስ ቃሉ የእግዚአብሔር እጅ ዛሬም አላጠረችም፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደትላንትናው ዛሬም ህያው ነው ይለናልና (ኢሳይያስ 59÷1 ዕብራውያን 13÷8)

### ብርቱ ጸሎት ያስፈልገናል

በዓለማችን ታሪክ እጅግ አስደናቂ የእግዚአብሔር ጉብኝቶች በግልም ሆነ በማህበር የሚገኙት በብርቱ እንደ እግዚአብሔር ቃል በሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለእናንተ ምጥ ይዞኛል ብሎ ለሚወዳቸው ምዕመናን የተናገረው ምን ያህል ሴት በምጥ ጊዜ እንደምታደርገው መቃተት እንደሚፀልይላቸው ለማሳየት ነው፡፡ (ገላቲያ 4÷49)

ሐናም በባህላቸው መሠረት ልጅ ያልወለደች ያገባች ሴት የሚደርስባትን ክፉ ስድብ መቋቋም ባለመቻሏና በመማረሯ በእንባ ሰካራም መስላ እስከምትታይ አነባች ጌታም መለሰላት፡፡

እግዚአብሔር ሳንጠይቀው ምን እንደሚያስፈልገን የሚያውቅ ደግ አምላክ ሲሆን ከአርሱ የእርሱን በረከትና ጉብኝት ለማግኘትም የሠጠን መመሪያ በጸሎት እርሱን መጠየቅ ነው፡፡ የገሀነም ደጆች አይቋቋሟትም የተባለች ቤተክርስቲያን ጌታ የጸሎት ቤት ብሎ የሰየማት በጸሎት የሚገኘውን በረከት ተከታዮቹ እንድንረዳ ነው፡፡ ስለዚህም እንደተሰጠን የክርስቶስ ቃል በግልም ሆነ ሁለትና ሦስት ሆነን ስንሰበሰብ ሁልጊዜ በፀሎት እንትጋ በፀሎት መለወጥ፣መንቃቃት፣መባረክና የሠይጣንና የዓለምን ስራ ማፍረስና ስጋንም መቀደስ በጌታ ይቻላል፡፡

(ማቴዎስ 21÷13 ዕብራውያን 4÷16)

ገና ከመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤተመቅደስና በስደቱ ዘመንም ምኩራብ የተዋቀሩት በአዲስ ኪዳንም የክርስቶስ ተከታዮች ህብረትን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጀምረው ቤተክርስቲያን የተዋቀረችው በብርቱ ጸሎት ነው፡፡

(የሐዋሪያት ሥራ 4÷31-36)

ቤተክርስቲያን በሠይጣን ተንኮል ተዳክማ ተከፋፍላ የሚያድነው የጌታ ወንጌል በተዳፈነበት ዘመንም ተሀድሶን የቀሰቀሰውና

ወደ ጥንቱ ወደ ክርስቶስ ቃል ወደ ፀጋው ወደ እምነት እንመለስ የሚለው ዘመንም ከገዳም በወጡት በነማርቲን ሉተር በነጆን ካልቪን በሀገራችን ኢትዮጵያም በነደቅ እስጢፎ ቀድሞ የተጀመረው በብርቱ ፀሎት ነበር፡፡

ዛሬም እግዚአብሔር ቃልን የሚፃረር ድርጊት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣የመንግስት መመሪያና የመገናኛ ዘዴዎች አሳች መግለጫና የእርኩሰት ትምህርትን ክርስቲያኖች በመመልከት ትውልድን ከሚመጣው ቁጣ መታደግ የሚችሉት በብርቱ ጸሎት በክርስቶስ ሀይል ብቻ ነው፡፡

በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ ፊቴንም ቢፈልጉ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ ከሰማይ ሆኜ እሰማለሁ.. እፈውሳለሁ (2ኛዜና 7÷14)

### ገሀነምን የሚያናውጥ ጸሎት

በጀንሰተኒ የቀረበ

በዚህ ዘመናችን ታላላቅ የእግዚአብሔር ጉብኝቶችና መነቃቃቶች የማናየው ብርቱ ጸሎት ስለጎደለብን እንደሆነ እገምታለሁ ዛሬ የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ዓለምን በሞላ ቤተክርስቲያን ነኝ የሚሉ አንዳንዶችንም ጭምር እያሣተ ብዎችን ወደገሀነም የሚመራው ለቤተክርስቲያን የተሰጣት የገሀነም ደጆች አይችሉዋትም የተባለውን እውን የሚያደርግ ብርቱ ጸሎት ስለጎደለብን ብቻ ነው፡፡

(ማቴዎስ 16÷18)

በቤተክርስቲያን የምናደርገው ስብከት ከጥልጊቱ ያለፈና ወደብዙዎች ወደዓለም ወዳሉት ሊደርስ የሚችለው በብርቱ ፀሎት ተዘጋጅቶ በብርቱ ጸሎት በሰሚዎቹና በሰባኪው በኩል ለሰዎች ከቤተክርስቲያን ግድግዳ ማዶ ላሉት መድረስ ሲችል ነው፡፡

ብርቱ ጸሎት በመንፈስ ቅዱስ መቃተት በቅዱስ ቃሉ የተመራ እንደ አስፈላጊነቱ በፆምና በሱባኤ የሚደረግ ነው፡፡ (ሮሜ 8÷26 ኤፌሶን 6÷18)

በቤተክርስቲያናችን ከብርቱ የጸሎት ጊዜ ይልቅ የብርቱ ስብሰባ ውይይት ጊዜ ሲበልጥብን ማስተዋል ያስፈልገናል፡፡ ውይይትና ስብሰባ መልካም ቢሆኑም አስቀድሞ አእምሮን የሚያበላሸውን ሰላም የሚደፈርሰውን ቅድስናን የሚያጎድለውን ነፍሰ ገዳይ ሠይጣንን በጸሎት ሳናሰርና ሳናባርር የምናደርገው ስብሰባ ሀሉ ፍሬቢስ ይባሱንም ቤተክርስቲያንን የሚያፈርስ የሚበትን መሆኑን በየራሳችን ቤተክርስቲያን በመንፈስ ዓይናችን ልንረዳ ይገባል፡፡

(ማርቆስ 3÷27 ያዕቆብ 4÷7)

በጸሎት ሰዎች ከሠይጣን እንደሚፈቱ በረከት ወደ አማኞች ኑሮ እንደሚገባ ቅድስና እንደሚሰፍን እንደቃሉ ልናምንበት ይገባል፡፡

ሌሎች በፀሎት እንደተሳካላቸው ስለሰማን ብቻ መፀለይ ሳይሆን መጀመሪያ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በቅድሱ ቃሉ እንደተፃፈልን በጸሎት ያገኙትን ድል አንብበን ልናምንበት የግድ ያስፈልጋል፡፡

ሰዎች ስለጠሩትና ስለተለማመዱት ብቻ እንለማመድ ማለት ለመላላጥ ይሆናልና ቃሉን አንብበን አምነን ለብርቱ ፀሎት መንፈሳችን ለአምሮአችንና አካላታችን እንዲነሳ በንስኃ ለመንፈስ ቅዱስ የተጋጀን እንሁን፡፡

“መንግስተ ሰማያት ቀርባለችን ንስኃ ግቡ”

(ማቴዎስ 3÷1) “በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህንን ዓለም አትምሰሉ” (ሮሜ 12÷2)

### የጸሎት ጥሪ

በሺልተን የቀረበ

የእግዚአብሔር የመቀደስ የማንፃት አንዳች ድርጊት ሊኖር የሚችለው በብርቱ ጸሎት ብቻ ነው፡፡ ቅዱሳት መጽሐፍት በትክክል እንደሚያስተምሩት በብርቱ ጸሎትና ጩኸት እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ሠምቶ እንደታደጋቸውና እንደባረካቸው ነው፡፡

እርሱም (ጌታም) በአንድ ስፍራ ይፀልይ ነበር በጨረሰም ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ ጌታ ሆይ ዮሐንስ ደቀመዛሙርቱን ጸሎት እንዳስተማራቸው እንፀልይ ዘንድ አስተምረን አለው፡፡

“እንዲህም አላቸው፡- ከእናንተ ማናቸውም ወዳጅ ያለው በእኩለ ሌሊትስ ወደ እርሱ ሄዶ ወዳጅ ሆይ ሶስት እንጀራ አበድረኝ አንድ ወዳጀ ከመንገድ ወደ እኔ መጥቶ የማቀርብለት የለኝምና ይላልን? ያም ከውስጥ መልሶ አታድክመኝ አሁን ደጁ ተቀልፏል ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ ተነስቼ

ልሰጥህ አልችለም ይላልን? እላችኋለሁ ወዳጅ ስለሆነና ተነስቶ ባይሰጠው እንኳን ስለነዘነዘው ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል፡፡

(ሉቃስ 11÷1-8)

ጌታችን እዚህ በምሳሌ የሚያስተምረን ስለብርቱ ፀሎት ነው፡፡ ብርቱ ፀሎት እምቢ የሚል መልስ አያገኝም፡፡

## የብርቱ ጸሎት ቅደም ተከተል

### 1. አስቸኳይ ጉዳይ

ለብርቱ ፀሎት አንድ አስቸኳይ ብርቱ ጉዳይ ይኖራል፡፡ በመጀመሪያ ያ አስቸኳይ ብርቱ ጉዳይን ሰዎች ያሳስባቸዋል፡፡ ክርስቶስ የሌላቸው በዓለም ጨለማ ያሉ ሰዎች ዛሬ የምናየውና የምንሰማው እጅግ የሚቀፍ ሐጢያት፣ጉቦ፣ሌብነት፣ዝሙት፣ውሸት፣ድግምት አስማት ወንጀልና የመሳሰሉት ለአንድ እውነተኛ ክርስቲያን እረፍት የማይሰጡ አስቸኳይ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ክርስቶስ የሌለባቸው ሰባኪዎች የመስቀሉን ሥራ ትተው የዓለምን ደስታና ብልፅግና የሚሰብኩ በሞሉበት ዓለም እውነተኛ የጌታ ልጆች ለብርቱ ጸሎት ይተጋሉ፡፡

### 2. ለሌሎች ይቅርና ርህራሄ

በየቀኑ በሥራ ቦታ በከተማችን የምናያቸው ክርስቶስ የሌላቸው በበሽታ በኃጢያትና በርኩሰት የተያዙ ሰዎች ፍቅር በእውነት ካለን ለብርቱ ጸሎት እንዘጋጃለን፡፡

ክርስቶስ የሌላቸው ዘመዶቻችን ወደገሀነም እንደሚነዱ ከተረዳን ለእነሱ ያለን ፍቅር ልንፀልይላቸው ግድ ይለናል፡፡ ፍቅር (ክርስቶስ የራሱን አይፈልግም (1 ቆሮ 13÷5)

### 3. አጣዳፊ ነገር ያተጋል

ማንም ሰው ጓደኛው ወይም ዘመዱ በእሣት ሲቃጠል ወይንም ጠላት ሊያርደው ሲገሰግስ ወይም ተርቦ ጠኔ ሊጥለው ሲፈለግ ዝም የሚል አይኖርም፡፡ በጥድፊያ ይደርስለታል፡፡

በክርስትናም እንደዚሁ ነው ዛሬ በየቤታችን፣ በየሠፈራችን፣ በየሥራ ቦታችን፣ ዛሬም በእውነተኛ ልብ በፆምና በፀሎት በጌታ ፊት ስንቀርብ ብዙዎች ከሠይጣን እየተፈቱ ወደ ክርስቶስ ይጨመራሉ፡፡

በየትምህርትቤታችን የምናያቸው ክርስቶስ የሌላቸው ሰዎችን ሠይጣን ሊያርዳቸው እንደሚነዳቸው ከተረዳን እኛ የክርስቶስ የሆንን ክርስቶስን ድረስላቸው ብለን ልንፀልይ እንጣደፋለን እንተጋለን፡፡

እኛ ክርስቲያኖች የምንፀልየው በፈጣሪያችን በአዳኛችን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስለታዘዝንና መልስም እንደሚሰጠን በቃሉ ስለተፃፈልን ነው፡፡

“እኔም እላችኋለሁ ለምኑ ይሰጣችሁማል ፈልጉ ታገኙማላችሁ መዝጊያውን አንኳኩ ይከፈትላችኋል የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልግም ያገኛል መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል፡፡”

(ሉቃስ 11÷9-10)

የተባረክሽው ጌታችን ኢየሱስ ክርቶስ ራስ ወዳድነታችንን ቀይረህ ለሌሎቹ እንድንደርስ እርዳን አሜን!

## ፆም ለፀሎት ሀይል ይጨምራል

ጸሎታችንን በፆም ካደረግን ወደ ትክክለኛው የፀሎት ህይወት መግባታችንን ያረጋግጣል፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በፆም ስጋቸውን ቢጎስሙና የጥሞና ሕይወታቸው ቢጎለብት እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን የማድረግ ባህርይ አለው፡፡

በጥንቷ ቤተክርስቲያን ፆምና የክርስትና እምነት አምዶች ውስጥ አንዱ ሆኖ ይሠራበት ነበር፡፡ በፆምና በፀሎት አያሌ የክፉውን ሠይጣን ሥራዎች እያፈረሱ ብዙዎች ወደ ክርስቶስ ማህበርና መንግስት ይገቡ ነበር፡፡ ዛሬም በእውነተኛ ልጆቹ ቃሉን በሚከተሉት ፆምና ፀሎት የሠይጣን ሥራ እየፈረሰ የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች እየተጨመሩ ነው፡፡ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ (እየፀለዩ) በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፡፡ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር (የሐዋሪት ሥራ 2÷47)

# ፅኑ ፀሎት

ስለፅኑ ጸሎት ከሚናገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱ መዝሙረ ዳዊት 142 ነው፡፡ በዚህ ክፍል ላይ መዝሙረኛው ንጉስ ዳዊት ብርቱ ጸሎትን ለምን ሊያቀረብ እንደበቃና እሱም ብርቱ ፀሎት የምናቀርብባቸውን በቂ ነጥቦች እናገኛለን፡፡ "ሕያው ሁሉ በፊትህ ፃድቅ አይደለምና" በአዲስ ኪዳንም ይህ ቃል ተብራርቷል "ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢያትን ሠርተዋልና" (ሮሜ 3÷23)

ወደ መንፈሳዊ መታደስና መነቃቃት የሚያደርሰውን የእግዚአብሔር ጉብኝት ሰዎች የሚያገኙት ኃጢተኛነታቸው ተሰምቷቸው በተሰበረ ልብ እግዚአብሔርን ሲፈልጉ ነው በቤተክርስቲያን ታሪክ ከመጀመሪያው ታላቅ ጉብኝት የጵራቅሊጦስ /ጴንጠቆስጤ/በዓለሃምሳ ጀምሮ የተከሰቱ ታላላቅ የእግዚአብሔር ጉብኝቶችና መነቃቃቶች ሁሉ የተከሰቱት በዚህ መንገድ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎች የዚህ አይነቱን የመንፈስ ቅዱስ ጉብኝት እንደሚፈልጉ የሚያደርጋቸው ሌላው ምክንያት ደግሞ የክፉ ሠይጣን ጥቃትና ዛቻ ናቸው፡፡

"ጠላት ነፍሴን አሳድዷታል ሕይወቴን በምድር ውስጥ አጎሳቅሏታል"

(መዝሙረ ዳዊት 142÷3)

የክርስቶስ ተከታዮች መንፈስ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በሙላት ከፈሰሰባቸው እለት በፊት በነበሩት ወራት ጠላት ሠይጣን ገዥዎችና ክፉ የሀይማኖት መሪዎችን አስነስቶ የታመኑበትን መሪ አሰቃይቶ ገድሎ እነሱንም ሊያጠፋ የተነሳበት ከፍተኛ የጭንቀት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታም ተጨንቀው በብዙ የምጥ ፀሎት ጌታን ሲጠይቁት የሰማይ መስኮቶች ተከፍተው የመንፈስ ቅዱስ ሀይል ወረደላቸው "በአንድ ልብ (በፀሎት) ሁሉም አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው" (የሐዋርያት ሥራ 2÷2)

በሀገራችን ኢትዮጵያም ያለፈው የደርግ መንግስት ወታደሮች ከተቃዋሚዎቹ ጋር በአዲስ አበባ ከተማ ጦርነት አድርገው ብዙ ደም ከመፋሰስ የተረፈው በግንቦት 1983 ዓ.ም ቅዱሳን ሁሉ በአንድ ልብ ሆነው ያደረጉትን ያም ጸሎት ጌታ ሰምቶ መሆኑን ተርጓሚው ይመሰክራል፡፡ ያ ፀሎትም በቀጣይ ብዙዎች ወደ ጌታ እንዲመለሱ አብቅቷል፡፡

# የብርቱ ጸሎት እንቅፋቶች (በቻርለስ ስፐርጂን)

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው በጎ ነገሮችን ለሰዎች ማድረግ ሲፈልግ ዘወትር እንቅፋት የሚሆኑም አሉ፡፡ ለመንፈሳዊ መታደስ እና መነቃቃት ትልቁ እንቅፋት በስሙ የተጠሩት የእግዚአብሔር ሰዎች አደራቸውን ረስተው እንቀላፊዎች ሲሆኑና በዓለምና በስጋ ነገሮች ተይዘው ለሠይጣን ሕቦቻቸውን አሳልፈው ሲሰጡ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ጌታ እግዚአብሔር እረኞች ብሎ የሚጠራቸውን በመሪነት ያስቀመጣቸውን ለሕዝቦቹ ግድ እንዲላቸው ዘወትር ከመምከር ከመገሰፅ ተቆጥቦ አያውቅም፡፡

"እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚጠብቁ እረኞች እንዲህ ይላል በጎቼን በትናችኋል አባርራችኋቸዋልም አልጎበኛችኋቸውም" (ኤርሚያስ 23÷2)

"እረኞች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እረኞቼም በጎቼን ስላልፈለጉ እረኞችም ራሳቸውን እንጂ በጎቼን ስላላሰማሩ በጎቼ ንጥቂያ ሆነዋልና ስለዚህ እርኞች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ በጎቼን ከእጃችሁ እፈልጋለሁ፡፡

(ሕዝቅኤል 34÷7)

እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ በጎች የሚቆጥር ስለሆነ በየጊዜው እረኞችን ይልካል እረኞች ታማኝ ካልሆኑም ያስወግዳቸዋል፡፡ እርሱም መልካም እርኛ መሆኑን በልጁ በክርስቶስ የገለፀውን የሚፈፅሙትን በየጊዜው ያስነሳል ይሾማል ይቀሰቅሳል፡፡ "የመንጋዬንም ቅሬታ ካባረርኋቸው ምድር ሁሉ ወደ በረታቸው ሰብስቤ እመልሳቸዋለሁ፡፡ እነርሱም ያፈራሉ ይበዙማል የሚጠብቋቸውን እረኞች አስነሣላቸዋለሁ" (ኤርሚያስ 23÷3)

"መልካም እረኛ እኔ ነኝ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል"

(የሐንስ ወንጌል 10÷11)

እረኝነት ለሁሉም የክርስቶስ ተከታዮች የተሰጠ የጋራ ሀላፊነት ነው፡፡ ዋናዎቹን እረኞች ቄሶችን ፓስተሮችን ጳጳሳትን ትልቁ ሀላፊነት ሲመለከታቸው እያንዳንዱ/ዷ ክርስቲያን አማኝ ደግሞ የወንድሙ/የወንድሟ የእህቱ/የእህቷ ነፍስ ጠባቂ ሆኖ በጌታ ተሰይሟል፡፡

መልካም እረኛ ለሚጠፉት ለተጎዱ ለወደቁ ግድ እንደሚለው ጌታ ክርስቶስ እንዳሳየን ለሌሎች ግድ የሚለን የምናፈቅር የምንፀልይላቸው እንድንሆን ክርስቶስ ኢየሱስ ይርዳን፡፡

# ዓለም አቀፍ የጸሎት ርእሶችና ምስጋናዎች

### በበርማ አዲሱ አዋጅ ያሰጋል

ቀድሞ በርማ በምትባለውና ዛሬ ሜንማር በተባለች ሀገር ከወታደራዊ አገዛዝ በኋላ ለውጥ እየታየ ነው፡፡ ሆኖም ግን አዲሱ የቡድሂስት ብሄርተኝነት ወደሌላ ሃይማኖት የሚገቡትን በህግ ለመቅጣት እያሰበ ስለሚገኝ ሁላችንም እንፀልይበት፡፡

### አዲስ የፋርሲ መጽሐፍ ቅዱስ

በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ የሚሠራጨው የክርስትና ሣተላይት ቴሌቪዥን የፋርሲ አዲስ መፅሀፍ ቅዱስ በኢራን መታተሙን አብስሯል፡፡

ፋርሲ በመካከለኛው ምስራቅና በሩቅ ምስራቅ አፍጋኒንስተን ደረስ የሚነገር ቋንቋ ስለሆነ ክርስቶስ ይህን በሚናገሩት ሁሉ ላይ እንዲነግስና እንዲምኑት እንፀልይ፡፡

### በኒጀር ክርስቲኖች እየተጠቁ ነው

የፈረንሳዩ የካርቶን ጋዜጣ መሀመድን በሚያንቋሽሽ ምስል ማወገዝ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በኒጀር ያሉ አክራሪ ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ ጥቃት ከፍተዋል፡፡

98 ከመቶ ሙስሊም የሆነበት ኒጀርን ክርስቶስ እንዲጎበኛትና በዚያ ያሉ ቅዱሳንን ጌታ እንዲጠብቅ እንዲያበዛ እንዲባርክ እንጸልይ ከወንጌል ሌላ ሙስሊሞችን ከሚያስቆጣ ጽሁፍ ንግግር እንቆጠብ፡፡

### ለሩማንያ ፕሬዚዳንት እንፀልይ

ድሮ ክርስቶስን የካደች ሩማንያ አዲስ ፕሬዚዳንት ዳግም የተለወደ ክርስቲያን ነው፡፡

ለዚህ ፕሬዚዳንት ሆነ በዓለም ሁሉ ላሉ መሪዎች እንደ ጌታ ቃል ሕዝባቸውን በፍቅር በፍትህና በእኩልነት እንዲመሩ እንፀልይ፡፡

### ለእስራኤልንና ለመካከል ምስራቅ ፀሎት

የክርስትና ምሳሌ ሆና ብዙ ለምትጠቀሰው እስራኤል ከኢትዮጵያ የሄደ ጥቁር አይሁድተ በዓል የሚደረግባቸውን ምድርና መላው መካከል ምስራቅ የሰላም ጌታ ክርስቶስ የተወለደባትና ያገለገለበትን አካባቢ ጌታ ከአመፅና ከደም እንዲጠበቅ እውነተኛ እስራኤል አዲሱ እስራኤል የክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ መሆናቸውን እየመሰከርን በፀሎታችን እንትጋ፡፡

### ልዩ የጸሎት መለኮታዊ ቃል

ስትፀልዩ ወደ እልፍኛችሁ/ጓዳችሁ ግቡ መዝጊያንም ዘግታችሁ በመንፈስ ቅዱስ በስውር ላለው አባታችሁ (ክርስቶስ) ፀልዩ በስውር የሚያይ አባታችሁ በግልጥ ይከፍላችኋል፡፡

ከማቴዎስ ወንጌል 6÷6 የተቀናበረ

# ልጆችን ለጸሎት ስለማዘጋጀት

ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም (ምሳሌ 22÷6) አዋቂ ክርስቲያኖች ዛሬ ላለንበት የክርስትና ህይወት ከወላጆቻችን ጀምሮ ቅዱስ ቃሉን በህይወት ያሳዩን ታላላቆቻችን አሉን፡፡

እኛም በተራችን ተተኪ ትውልድ በሚያድነው በሚባርከው የክርስቶስ ቃል እንዲፀኑ በቃልና በተግባር የመምራት ሀላፊነት አለብን፡፡

ዛሬ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ልጆች የሠይጣንና የተከታዮቹ ዓላማ ሆነው በችግር ላይ መሆናችን የአደባባይ ጉዳይ ነው፡፡

የሚድያ ውጤቶች፣ ፋሽን፣ ዘፈን፣ በትምህርት ቤት ሳይቀር የሚሰጣቸው ነገር ከክርስቶስ ቀና የቅድስና ትምህርት የሚያስክድ ዓለማዊ ጉዳይ ዘመን ላይ ነን፡፡

ታዲያ በዚህ ክፉ ዘመን ልጆቻችን የክርስቶስን ቃል አምነው እንዲፀኑና ለሌሎች እንዲተርፉ ምን መደረግ አለበት? መልሱ አንድና አንድ ነው ልጆቻችንም በአዳም መተላለፉ ኃጢያት ስላለባቸው በቅዱስ ቃሉ እየተመሩ ሊያድጉ በቃልም በኑሮም ወላጆችና ታላላቅ ዘመዶች ልንከባከባቸው ይገባል፡፡

በአእምሯችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ክፉውን ዓለም አትምሰሉ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ለልጆችም ጭምር ነው፡፡ (ሮሜ 12÷2)

ልጆችን ለፀሎት ለማዘጋጀት ቀዳሚ ነገር በቅዱስ ቃሉ መላው ቤተሰብ መኖርና መፅናት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቂቱ ትዕዛዝ ምንድናት ተብሎ ሲጠየቅ የሠጣቸው መልሶች እግዚአብሔር አምላክን በሙሉ ሀይል መውደድና ማምለክ ባልንጀራና ጎረቤትን እንደእራስ መውደድ ከልጆች ጭምር መላ ቤተሰብ ሊጠብቀው ያስፈልጋል (ማቴዎስ 22÷35)

ለልጆቻችን ምግብና ልብስ እንደምንጠነቀቅ ሁሉ ከሁሉ ለሚበልጠው ነፍሳቸው ደግሞ የሚጠቅመውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲመገቡ እናድርግ (ማቴዎስ 4÷4)

ቅርንጫፉ በግንዱ ላይ እንደሚኖር ቅርንጫፉ እኛም ልጆቻችንም በየዕለቱ በቅዱስ ቃሉና በጸሎት በግንዱ በክርስቶስ ላይ ስንኖር ህይወታችን ይለመልማል፡፡

እራሳችን የማንፈፅመውን ለልጆቻችን አንዘዝ ስህተትንና ይቅርታ መጠየቅንም ልጆችን ሊያስተምር ያሻል፡፡

በዘመናችን በነጭና በጥቁር በአንዱ ጎሳና በሌላው መካከል ያለ ከዘር ወደዘር የሚተላለፉ በጥላቻ ኃጢአት ስለሆነ በይቅርታ ልጆቻችንን ከመርገም እንታደግ እምነትና መዳን ከነመላው ቤተሰብ መሆኑን አውቀን እንለማመደው (ሐዋሪያት 16÷31)

## ልዩ መልዕክት ከተርጓሚውና ቤተሰቡ በኤዲ (አደፍርስ) ሀብቴ መካሻ

### እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ *(የሐዋርያት ሥራ 1÷8)*

የተወደዳችሁ የምጽዐቱ አንባቢዎች እነሆ ተርጓሚው ኑሮዬን በምድር አሜሪካ ካደረግሁ ሁለትሽ ሱባኤ (አስራ አራት ዓመት) ሊሞላኝ ሲሆን ውድ ባለቤቴና ልጆቼ ከመጡልኝ ስምንት ዓመት አገባድጃለሁ፡፡

በእነዚህ ሁሉ ዘመናት በምህረቱ ብዛት የጠበቀኝ የረዳኝ የመራኝ የባረከኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ይሁን አሜን፡፡

ይህን ትርጉም ስራ እንድጀምር ጌታ የላካቸው የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የሠንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለአሜሪካዊ አሳታሚ የላኩት ምስክርነትና በአዲስ አበባ መካነየሱስ የሥነ ፅሁፍ አገልግሎት ለተሰጡኝ ማበረታቻዎች ጌታ የተመሰገነ ይሁን ህትመቱ እንዲቀጥል የተባበሩኝን ሁሉ ባለቤቴ ፋንታየ ግርማን ልጆቼን ቀዳማዊትና ሥምረትን የወቅቱ የኢትዮጵያ አስተባባሪ እህታችን አልማዝ አሳየን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በዚህ የትርጉም አገልግሎት አያሌዎች የተፅናኑ ክርስቶስ ከሌለበት ሃይማኖት ወደ ክርስትና የገቡና በክርስትና ሃይማኖት ሆነው ክርስቶስን ጌታ ያላደረጉ ፀንተዋል ተለውጠዋል ታድሰዋል፡፡ ክብር ለብቸኛው አዳኝ ክርስቶስ ይሁን፡፡ ወደ አሜሪካ ካቀናሁ በኋላ ትርጉሙን እንዲቀጥሉ ጥያቄ ያቀርብኩላቸው ወገኖች ሊቀጥሉት ስላልቻሉ እኔው እራሴና የሥራና የቤተሰብ ሀላፊነቴን ጨምሬ ልቀጥለው እነሆ አሜሪካ ከመጣሁ አምስተኛውን ትርጉም ልኬያለሁና ጌታ ለመታደስ ለመታነፅ ለመባረክ ያድርገው፡፡

የምጽዓቱ የምስራች አሣታሚዎች በመጠን የሚኖሩ ለመሆናቸው ቤታቸው ሄጄ ያየሁ የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ይህን ትርጉም በኢትዮጵያ ለሚሠሩ ብዙ መክፈል ቢወድዱ ነገር ግን ገቢያቸው የተወሰነ በመሆኑ እነሆ አሁንም በበጎ ፈቃድ ያቅሜን እንድቀጥል ፀልዩልኝ አስተያየትም ላኩልኝ፡፡

አሜሪካ ከመጣሁ ትምህርቴን እየተማርኩና ከተመረቅሁ በኋላ ጌታ በእጄ ጥምቀት ሶስት ደርዘን የሚጠጉ ነፍሳት ከአፍጋኒስታን ከቢታን ኔፓልያ ከምዕራብ አፍሪካና ኩናማዎች ፀልዩልኝ ገና ብዙዎችን እንደርሳለን ዘወትር ምልጃችሁ አይቋረጥ፡፡

### ልዩ ማሣሰቢያ

ለህትመቱ ሥርጭትና ድጋፍ የአቅማችሁን ለእህታችን አልማዝ አሣዬ መላክ ትችላላችሁ

የምጽዐቱ የምሥራች ወንጌል አገልግሎት

የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ

**ኢትዮጵያ**

### የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል

### መነቃቃት አገልግሎት

ዋና አሳታሚ ሪክ ካርማይክል

ተርጓሚ፡ኤዲ/ሄዳፋርስ ሀብቴ መካሻ

አስተባባሪ አልማዝ አሳዬ

የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ

**ኢትዮጵያ**